# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)

Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## ታሪካችን ከሚጠፋ አጥፊው ወያኔ ይጥፋ

ኢትዮጵያኖች ነን ብለን ስሟን መጠሪያችን ያደረግነው ለስሟ መጠርያ ቁና ማሰፋታችን አይደለም። የአያትና የወላጆቻችን የኛም ጭምር አፀመ እርስታችን ነችና ለሷ የምንሳሳው ህይወት የለንም። የወጣት ክንፍ ድርጅታችን ሆነ ቀደምቶቻችንም አምጣ የወለደች ኢትዮጵያ ነችና ሊያጠፋት የመጣን ተምች በደንብ አድርገን እንደ ተርብ እነነድፈዋለን። ቅጥረኛነትን እንደሙያ የተካነባት ቆሻሻው የወያኔ ስርዓት የጣር በትር በታሪካችን ላይ አብዝቷልና የምናስቆመው በባእዳን የፖለቲካ መሃንድሶች ሳይሆን እኛ ነን ብለን የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ) አባላቶች በኩራት እንገልፃለን። ይህ ደግሞ ከአፍ ላይ ነፋስ የሚወስደው ከንቱ መሃላ ሳይሆን ነገ በጅ የሚዳሰስ እውነት ነውና ኩራቱን እንደግመዋል።

ዛሬ መቃብሩ የተቆፈረለት መግነዙ የተዘጋጀለት ነገ የታሪክ ትብያነቱ የተራገገጠለት ወያኔ  ሐርነት ትግራይ ስርአት ዛሬ በሃይማኖቶች ላይ፣ በዋልድባ፣ በአሰቦት፣ በዝቋላ ላይ እየለቀቀ ያለው እሳትና ግሬደር ዛሬ በታላላቅ ሐይማኖቶች ላይ እየመዘዘ ያለውን ዘረኛ ጎራዴ እኛም የኢትዮጵያ ወጣቶች የማይደንዝ ኢትዮጵያዊ ሠይፍ ሆነን ታሪካችን ከሚጠፋ ታሪክ አጥፊው ወያኔ ይጥፋ ብለን ተነስተናል።

## ለኢትዮጵያ ወጣቶች ጥሪ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ ድርጅት ለጠቅላላው ወጣት ጥሪ የምናደርገው ገጥመን በታሪካችን ላይ ሠደድ የለቀቀውን ወያኔ እናሳደው ነው።  ሌላ ጥሪ ካደረግንማ ለጠላት የተጠንቀቅ ጥሪ ይሆናልና በመንፈሳችንም በአካላችንም  እንከታታለው። በማጠቃለያም በአሁኑ ሰዓት ለሃይማኖትታችን፣ ለታርካችን፣ እንሰየፋለን ላሉ አባቶቻችን ከጎናቹሁ ነን ሳይሆን ከፊታቹሁ ያድርገን ዘንድ በፀሎት አትርሱን እያልን ሙሉ ድጋፋችንን በሃገር በውስጥም ያለውን የኢህአፓ የታሪክና የጀግንነት ውልድ የሆንነው ወጣቶች እየገለፀን በወያኔ እሳት በሚተፋ ብረት ፊት ቆማቹሁም ለሀገራችንና ለሃይማኖታዊ  መብታችሁ እየታጋፈጣችሁ ላላችሁ ኢትዮጵያዊ ሙስሊሞች  ጥያቄያችሁ ጥያቅያችን ነውና ከውስጣችሁም ከውጪም ከናተው ጋር ነን ስንል ድጋፋችንን እንገልፃለን።

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl

Ethiopia Will Prevail!